# በሙያ ላይ የታወጀ ጦርነት

በሙለታ በዳሴ

*የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች በቅርቡ ባስነበቡን ርዕሰ አንቀጽ ጋዜጣቸው ሚዛናዊ እንዳልሆነች እና ሌላ ማንኛውም ጋዜጣም ቢሆን ሚዛናዊ መሆን የማይጠበቅበት መሆኑን የሚያሳይ አቋሚቸውን ግልጽ አድርገውልናል፡፡ እርግጥ ነው ጋዜጣ ሚዛናዊ እንዲሆን የሚያስገድድ ድንጋጌ በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ አለመኖሩ ግልፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሚዛናዊነት የህግ ግዴታ አለመደረጉ የስነ - ምግባር ወይም የሙያ ግዴታነቱን ያስቀረዋልን? ጋዜጦችስ ሚዛናዊ እንዲሆኑ የሚያስገድዷቸው ንድፈሃሳባዊ፣ ፍልስፍናዊ፣ ስነምግባራዊና ሞራላዊ ዳራዎች የሉምን? የሚሉ ምክንያታዊ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም፡፡ ወደፊት የኢትዮጵያ የፕሬስ ውጤቶች ዓይነተኛ መገለጫ ይሆናሉ ብዬ ከማስባቸው ከእነዚህ እሴቶች ጋር የተያያዙ አንዳንድ ነጥቦችን በማንሳት በጉዳዩ ላይ ያለኝን አስተያየት ለማቅረብ እሞክራለሁ ፡፡ በመሆኑም ሚዛናዊነትን ከሙያተኝነት (professionalism)፣ በጋዜጠኝነት ሙያ እውነታን የመፈለግ ሂደት እንዲሁም በዚህ ሂደት ላይ የየራሳቸውን ተፅእኖዎች ከሚያሳድሩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ጋር የተያዘ ትንተና በማቅረብ በአዲስ ነገር አዘጋጆች በ መስከረም 9 ቀን 2002 ኣ.ም በወጣውና "**አዲስ ነገር ሚዛናዊ አይደለችም** " በሚል ርእስ ስር በቀረበው ርእሰ አንቀፅ ላይ ያንፀባረቁትን አቋም ኢ. ምክንያታዊነት እንደሚከተለው ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡*

1. ***ጋዜጠኝነት እንደ ሙያ (ፕሮፌሽን)***

   *ጋዜጠኝነት ሙያ (ፕሮፌሽን) ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጥያቄ በኮሙዩኒኬሽን ሳይንስ ውስጥ እጅግ አጨቃጫቂ ከሚባሉት ጉዳዮች ተርታ ለብዙ ጊዜ ተመድቦ ቆይቷል፡፡ እንደ ሶሾዮሎጂስቶች እምነት አንድ ስራ ሙያ (Profession) ነው ለመባል የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ መገኘት*

ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም አንድ ሙያ ሙያ ተብሎ ይጠራ ዘንድ በሙያ ገበያ ውስጥ በሌላ ሙያ አባላት ሊቀርብ የማይችል በሞኖፖሊ የተያዘ አገልግሎትና ይህን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አባላቱ ብቻ የሚካኑት የተደላደለ እውቀት እንዲኖረው ያስፈልጋል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህብረተሰቡ አገልግሎቱን ማግኘት የሚችለው ከሙያተኞቹ ብቻ እንደሆነ መቀበል ይኖርበታል ፡፡ አገልግሎቱን አስመልክቶ በሙያው አባላት መሃከል ውድድር ይኖር እንደሁ እንጂ በሙያዎች መሃከል የሚኖር ውድድር መኖር የለበትም ፡፡ እንዲህ መሰሉ ውድድር ከተከሰተ የሙያው የግንዛቤ መሰረት (cognitive base ) በበርካታ መስኮች መሀል የይገባኛል ውዝግብን ያስከትልና የአገልግሎቱን ተገቢነት (legitimacy)እና የአገለግሎት አሰጣጥ ዘዴዎቹን ጥያቄ ውስጥ መጣሉ የማይቀር ይሆናል፡፡ ስለሆነም ሙያዎች በሚሰጡት አገልግሎት ላይ ያላቸውን ብቸኛ ቁጥጥር ለማረጋገጥ የሙያውን የግንዛቤ መሰረት ማጥብቅ ይኖርባቸዋል ፡፡ ይህን ማድረግ ይችሉ ዘንድ ደግሞ የሙያ ስልጠናዎቹ የይዘትና የጥራት ደረጃ (standardized professional training ) ወጥነት እንዲኖረው ያደርጋሉ ፡፡ በርካታ ሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ እውቅና በሚያገኙ ከፍተኛ የሙያ ማሰልጠኛ የትምህርት ተቋማት(አክሬዲትድ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ) አማካይነት የሙያ ስልጠናዎቹን ይቆጣጠራሉ ፡፡ እነዚህ የሙያተኛ ማሰልጠኛ ተቋማት ወደፊት መስኩን የሚቀላቀሉ ሙያተኞች የሙያውን የእውቀት መሰረቶች በሚገባ መገንዘባቸውን፣መካናቸውንና መቀበላቸውን ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በሙያተኞቹ የሚሰጡት አገልግሎቶችና ምርቶች ደረጀቸውን የጠበቁ (standardized) እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የጎላ ሚና ይጫወታሉ ፡፡ ሙያዎች በእነዚህ ተቋማት አማካይነት የሚያገኙት ጥቅም በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም ፡፡ ተቋማቱ የሙያው አባላት በሙሉ የስልጠኑባቸውን ቴክኒኮችና የአሰራር ስልቶች ከሙያው ከፍተኛ አላማዎችና ግቦች ጋራ አጣጥመው መተገብር የሚችሉበትን ክህሎት በማስጨበጥ ረገድ የሚያደርጉት የጎላ አስተዋፅኦ አለ ፡፡ ሙያውን አስመልክቶ የተሰሩ በርካታ የሶሲዮሎጂ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሙያዎች በህብረተሰቡ ዘንድ በላቀ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ ተደርገው ይታያሉ ፡፡ ለዚህ አይነቱ ማህበረሰባዊ እውቅና መሰረተ መነሻ ምክንያቱም ሙያዊ ው አገልግሎቶችና ምርቶች ሁለንተናዊ

ተደራሽነት ያላቸው በማህበራዊ አወጣጥ ፣ በፖለቲካዊ አመለካከት ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት የአገለግሎት ልዩነት የማያደርጉ ሆነው መገኘታቸው ነው ፡፡ የሙያው ንድፈ ሃሳባዊ እውቀትና የግንዛቤ መሰረት ዋነኛ አላማም አገልግሎቱ ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ ሙያው ለህዝባዊ ይሁንታው መሰረት የሆነውን ይህን የፍትሃዊነትና የሚዛናዊነት ገፅታ በአገልግሎቶቹ ውስጥ ሁሌም እንዲያንፀባርቅ ማድረግ ነው ፡፡

ከዚህ አንፃር ጋዜጠኝነት ለስራው አስፈላጊ የሆነና በሌሎች ሙያዎች የይገባኛል ውዝግብን የማያስነሳ ፣ ከሌላ መስክ በመፍለስ መስኩን የሚደባለቁም ሆኑ በስራው ላይ የተሰማሩ አባላቱ በስራ ላይ በሚሰጥ ስልጠናም ይሁን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኩል ይካኑት ዘንድ የግድ የሆነ የተደላደለ የእውቀትና የግንዛቤ መሰረት ያለው አንድ ሙያ መሆኑን መረዳት አስቸጋሪ አይሆንም ፡፡ በስልጠና የሚገኘው ክህሎት ጋዜጠኞች በአገልግሎት አሰጣጡ ሂደት ውስጥ ለምሳሌ በዜና ዝግጅት ሂደት የፍሬ ነገሩን የዜና ብቃት ፣ሚዛናዊነት፣ የምንጩን ትክክለኛነት ወዘተ መሰል ጉዳዮችን በሙያው የቴክኒክ መስፈርቶች መሰረት ለመወሰን የሚችሉበትን የውሳኔ ነፃነት ያጎናፅፋቸዋል፡፡ በተጨማሪም ጋዜጠኝነት እንደሙያ ያበጃቸውን ከፍተኛ አላማዎችና ግቦች በአባላቱ ዘንድ መከበራቸውን የሚያረጋግጥበት የስነምግባር ደንብም አለው ፡፡ ከሞላ ጎደልም ለአባላቱ የሙያ ስልጠና(የስራ ላይ ስልጠናመ ሊሆን ይችላል ) በሚሰጡና የብቃት ማረጋገጫ ባገኙ የማሰልጠኛ ተቋማት አማካይነት የሙያ አገልግሎቱን የደረጃ ወጥነት የሚያረጋግጥበት አሰራረ ያለው የስራ መስክ ነው ፡፡ ጋዜጠኝነት አገልግሎቶቹን ለጠቅላላው ህብረተሰብ ( በተመረጡ ጉዳዮች ላይ የተለየ አትኩሮት የሚሰጡ ህትመቶችም ሳይቀሩ ) የሚያቀርብ የስራ መስክ ነው ፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል በዝርዝር የተመለከቱትን ሁሉንም መስፈርቶች የሚያሟላ መስክ በመሆኑ ጋዜጠኝነት አፍን ሞልቶ ሙያ (Profession) ነው ለማለት ይቻላል፡፡

በሌላ መልኩ ጋዜጠኝነት (Profession) የመስኩን ማህበራዊ ይሁንታ እና የአባላቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚከተላቸው ስልቶች የመስኩን

ሙያነት ለማረጋገጥ እንደሚያግዙ ተጨማሪ ማሳያዎች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ ጋዜጠኞች የሙያ ክንውኖቻቸውን በሙያው የስነምግባር ደንብ መሰረት መፈፀማቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ተአማኒነት በመገንባት ማህበራዊ ተደማጭነታቸውን አጠናክሮታል፡፡ በተጨማሪም በሚሰጡት አገልግሎት ላይ ከጣልቃ ገብነት የፀዳ የተሟላ ቁጥጥር ሊያገኙ የሚችሉበተን ሁኔታን ከማመቻቸቱም በላይ የገቢያቸውን ዝቅተኛ ወለል በየገዜው ለማሳደግ አስችሏቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ጋዜጠኝነት የሙያ (Profession) ደረጃን መጎናፀፉ ለአባላቱ ከላይ የተገለፁትን ጥቅሞች እንዳስገኘ ጥርጥር የለውም፡፡

ስለሆነም ጋዜጠኝነት በሚሰጠው አገልግሎት (በተለይ ከምንነጋገርበት የሚድያ ዘርፍ ጋር ተያያዥ በሆኑት የዜና እና የፊቸር ስራዎች) እንደማንኛውም ሙያ በፖለቲካ ወገንተኝነት ያልተቀነበቡ ሁሉን አቀፍ ማህበራዊ አገልግሎቶችን አከናዋኝ ተደርጎ እንዲወሰድ በማድረግ ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ ካላቸው የሙያው እሴቶች መሃል ቀዳሚውና ዋነኛው እሴት ሚዛናዊነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሚዛናዊነትን መሰል እሴቶች ጋዜጠኝነት በጥብቅ አክብሮ የሚንቀሳቀስባቸው የማይጣሱ ቀይ መብራቶች ተደርገው የሚወሰዱትም ለዚህ ነው፡፡ እነዚህ የሙያና የስነምግባር እሴቶች መኖራቸው በአንድ በኩል የአገልግሎቱን ሁለንተናዊነት የሚያሰናክለውን አድልዎና ወገናዊነት ለመቆጣጠር ሲጠቅም በሌላ በኩል ጋዜጠኞች እራሳቸውን ለላቁ ማህበራዊ ፋይዳዎች የቆሙ ሙያተኞች (Professional) አድርገው እንዲመለከቱ አስችሏቸዋል፡፡ በብዙዎች የሙያው አባላትና የመገናኛ ብዙኀን ጠበብት ዘንድ ሚዛናዊነት ለሙያ ስራዉ የሚያስፈልግ ጠቃሚ ቅድመ ሁኔታ (essential condition of work) ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ከዚህ በተቃራኒው ‹‹የአዲስ ነገር›› ጋዜጣ የሚዛናዊነት እሴትን ታላቁን ሙያ እንደበከለ አንዳች ተስቦ አድርጎ መቁጠሩ አዘጋጆቹ ከራሱ ከሙያው ጋር ያላቸውን ሁነኛ ተቃርኖ አመላካች ነው፡፡ ሚዛናዊነት አይጠበቅብንም የሚለው ይህ የአዘጋጆቹ አቋምም ጋዜጠኝነትን እንደ ሙያ (Profession) ካለመቁጠር የመጣ ከመነሻውም ግዙፍ ግድፈት ያለበት የተሳሳተ አቋም ነው፡፡ ጋዜጠኝነት

እንደ ሙያ (Profession) ከሚከተላቸውና ከሚያከብራቸው አንኳር እሴቶች አንዱ ሚዛናዊነት መሆኑንም እንደሚከተለው አሳያለሁ ፡፡

2. **ጋዜጠኝነት - እንደ እውነት መፈለጊያ መንገድ**

የአንድን ክንዋኔ እውነታ ማወቅና መናገር የጋዜጠኝነት ሞያ ግብ ነው፡፡ ነገር ግን እውነት ምንድነው? በምንስ መንገድ ነው የሚገኘው? የሚለው ፍልስፍናዊ መጠይቅ ተመሳሳይ እውነትን ( ፍሬነገርን ) መነሻ ባደረገ ንድፈሃሳባዊ መሠረት ላይ እንደተገነቡ ሌሎች ሙያዎች ሁሉ በጋዜጠኝነት ሙያም ውስጥ የሚመላለስ ስነ - እውቀታዊ መጠይቅ ነው፡፡ እውነትን በስነ - እውቀት (epistemology) ዘርፉ አማካኝነት ለመፈለግ ደፋ ቀና በሚለው ፍልስፍና ውስጥ ጉዳዩ አወዛጋቢ ሆኖ የቀጠለና የሚቀጥል ይሁን እንጂ በተግባራዊ የሳይንስ ዘርፎችና ሙያዎች ዘንድ ግን እውነት ተጨባጭነት ያለውና ሊደረስበት የሚችል ነባራዊ ሁኔታ ነው የሚለው ግምት የሙያዎቹ ንድፈ ሃሳባዊው መሰረት (cognitive basis) መንደርደሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ፍልስፍናን በመሰሉ መስኮች ‹የእውነትን› ፅንሰ ሃሳባዊና ተግባራዊ ውሰንነት አስመልክቶ የሚነሳው ውዝግብ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨባጭ የሚገኝና የሚነገር እውነት አለ የሚለው እምነት የሁሉም ሙያዎች ንድፈ ሃሳባዊ መነሻ ነው፡፡ የሶሲዮሎጂ ጠበብቶች በጋዜጠኝነት ሞያ ውስጥ ደግሞ እውነት የሚደረስበት መንገድ በሚዛናዊነት ባህል በኩል እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡ ሚዛናዊነት ለዚህ አይነቱ አገልግሎት ብቁ ሆኖ የተገኘው በተግባራዊው የህይወት ሂደት ውስጥ የጋራ ስምምነት የተደረገበትን ወይንም የተለመዱ መለኪያዎችን መሰረት ያደረገ በመሆኑና ሁሉን አይነት ተነፃፃሪ እይታዎች አካታች በመሆኑ የተነሳ ነው፡፡ እዚህ ላይ መነሳት ያለባቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች ሚዛናዊነት ስንል ምን ማለታችን ነው? ሚዛናዊነትን የሚፈታተኑ ነገሮችስ ምንድን ናቸው? የ‹‹አዲስ ነገር›› አቋምና አሰራርስ ከዚህ አንፃር እንዴት ይታያል? የሚሉት ናቸው፡፡

**ሚዛናዊነት ስንል ምን ማለታችን ነው?**

የሚዛናዊነት መነሻ እውነትን ከእራሳችን እይታ መለየት ይቻላል፤ እናም ጋዜጠኞች ይህን እውነት በገለልተኝነት የሚያስተላልፉ ባለሞያዎች ናቸው የሚለው ጠንካራ አስተሳሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ አስተሳሰብ አንፃር ሲቃኝ ሁለመናው በፍሬነገር ዘገባና በእሴታዊ ብያኔዎች (value judgments ) መሀከል ያለውን ቀጭን መስመር መለየት እስኪሳነው ድረስ በጥልቅ ግላዊ አመለካከት እና ርዕዮት የታጀለ ጋዜጠኛ ለሚዛናዊነት ፀር እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የሚዛናዊነት መነሻ የጋዜጠኛ ዘገባ ሚዛናዊና ሁሉንም እይታዎች /perspectives/ ያካተተና ማህበራዊ እውነታን ማንፀባረቅ አለበት የሚለው የሙያው ንድፈ ሃሳባዊና ስነ - ምግባራዊ መርህ ነው፡፡ ጋዜጠኝነት የተለያዩ እይታዎችንና ሃሳቦችን በሚዛናዊነት ማስተናገድ አለበት የሚባለው አንባቢው እውነትን የሚያገኘው ከተለያዩ ሃሳቦችና እይታዎች ፍጭት ነው የሚል ጠንካራ የሙያው ርዕዮተ አላማዊ ግንዛቤ በመኖሩ ነው፡፡

በመሆኑም ጋዜጠኛው የራሱን ግላዊ እምነት ሳይጨምር አንድን ክስተት ወይም ሁነት የሚመለከቱ ዘገባዎችን የነገሩን የተለያዩ ገፅታዎች ኩነቱ ከተከናወነበት ማዕቀፍ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርበታል የሚል የሙያው ተግባራዊ እሳቤ አለ፡፡

በተመሳሳይም አንድ ጋዜጠኛ በሚዛናዊነት ልኬት ዜናን ኢያዛባም ሲባል መነሻው እውነት ሊደረስበት የሚችል ነገር ነው፣ ጋዜጠኞች በክንውኑ ገለልተኛ ተመልካች ናቸው፣ የሚዘገበው እውነት የእነሱን ግላዊ ፍላጎት ወይም ስነ-ምግባራዊ አቋም እንዲያካትት ሳያደርጉ መዘገብ ስለሚችሉ በአንድ ቦታ ላይ እየተደረገ ያለውን ጉዳይ አስመልክቶ በገለልተኝነት ሚዛናዊ ዘገባን መዘገብ ይኖርባቸዋል የሚል ጠንካራ ሙያዊ እና ስነ-ምግባራዊ መነሻ መኖሩን ከአዲስ ነገር አዘጋጆች በስተቀር ለማንም ባለሙያ የተሰወረ ሐቅ አይደለም፡፡

ይህ ሲባል ታድያ ጋዜጠኝነት እንደ ሙያ አዘጋጆችና ጋዜጠኞች የሚምኑበትና እና የሚከተሉት ፖለቲካዊ ወይም ርእዮተ አለማዊ አቋም መኖር የለበትም የሚል አቋም አለው ማለት እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በአመዛኙ  የጋዜጦች የርእሰ አንቀፅ አምዶች ወይም የአስተያየት አምዶች እንዲህ መሰሉን የጋዜጣዋ ባለቤቶችና አዘጋጆች ፖለቲካዊ አቋም  የሚስተናገዱባቸው የህትመቱ ክፍሎች ናቸው ፡፡ ይህም እንኳ ሆኖ በተለይ በንግድ ሚድያነት አገልግሎታቸውን ለጠቅላላ አንባቢ የሚያቀርቡ ህትመቶች ከጋዜጣዋ አዘጋጆች በተፃራሪ የቆሙ አስተያየቶችንም ጭምር ይዘው በመውጣት የአንባብያንን ፈርጀ ብዙ ፍላጎቶች ለማንፀባረቅ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ፡፡ ለዚህ አይነቱ የሙያ መተክል መነሻ የሆነው ዋነኛው ምክንያትም  እንደ አንድ ዴሞክራሲያዊ መድረክ የተፎካካሪና ተቀናቃኝ  ሃሳቦችን  የመስማት እድል ማክበርና አንባቢያን ሁሉንም  አመለካከቶችና እና እይታዎች ለማወቅ ያላቸውን መብት ጋዜጠኝነት ማክበር ስላለበት ነው፡፡

ከዚህ በተቃራኒው መስራት ይህን የዜጎች መሰረታዊ መብት በመጋፋት ጋዜጣው የሚደግፈውን ሃሳብ ብቻ ይዞ ወደ አደባባይ መውጣትን ተቃራኒ አመለካከቶችን ማፈንን ያስከትላል ፡፡ ይህን የዴሞክራሲያዊ ፕሬስ መሰረታዊ የሙያ መርህ በአደባባይ በመረሸን ሚዛናዊ አልሆንም ብሎ መለፈፍ ለአንባቢያን ያለ ንቀትን ያሳያል ፡፡ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል፣ አንድ አይነት አቋምና አስተያየት ብቻ ማላወሻም ሆኗል እያሉ ነጋ ጠባ መንግስትን ሲከሱ የሚውሉት የአዲስ ነገር አዘጋጆች ለሚያቀነቅኑት ሃሳብ ታማኝ አለመሆናቸውን ይፋ ያወጣ  ድርጊት ነው ፡፡

በሚዛናዊነት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ምክንያቶችን በአጭሩ ቃኝተን ‹‹አዲስ ነገር›› ከዚህ አንፃር በሙያ ሽፋን ካጨቀቻቸው ግሳንግሶች ጋር  ምን መስላ እንደምትታይ ለማየት እንሞክራለን ፡፡

በሚዛናዊነት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ምክንያቶች በሶስት ፈርጆች ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ

ሀ) ተቋማዊ ሁኔታዎች (Organizational factor)

ለ) ኢንዱስትራዊ ሁኔታ እና

ሐ) የእያንዳንዱ ጋዜጠኛ አቋም ናቸው

አንድ ጋዜጣ ተመሳሳይ የፖለቲካ አቋም፣ ተቀራራቢ እድሜ፣ ከአንድ አካባቢ በመጡ፣ ተመሳሳይ እምነት ባላቸውና ተቀራራቢ የትምህርት ደረጃ፣ ባላቸው ልምድ አልባ ጋዜጠኞች ከታጨቀ አባላቱ በተሟላ የሙያ ስልጠናና የሥራ ልምድ ሊካበት የሚገባውን የሙያውን መሰረታዊ አስተምህሮት ለመጨበጥ እና ተግባራዊ ለማድረግ ያላቸው እድል አናሳ ይሆናል፡፡ በጋዜጠኝነት ክንውን ውስጥ መሰረታዊ የሆነውን ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ የሚያስችል መሰረታዊ የሙያ ክህሎትና የልምድ እጥረት ባለበት በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሚዛናዊ የሃሳብ ፍጭትና ገለልተኝነት በጋዜጣው ውጤቶች ውስጥ ሊንፀባረቅ አይችልም፡፡ ከዚህ በበለጠ ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች በተጨማሪ በጋዜጣው ላይ የሚሰሩት ጋዜጠኞች የጎጥ ፖለቲካ ሰቢኪ መሆን የሚሹና ጋዜጠኝነትንም ለዚህ ግባቸው ማስፈፀሚያ መሣሪያ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ጋዜጠኞች ሲሆኑ የሚዛናዊነት ጉዞ ፍትሃት ተጀመረ ለማለት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በሀገራችን የግሉ የሚዲያ ኢንዱስትሪ በበርካታ ችግሮች የተተበተበ ነው፡፡ በኢንዱስትሪው ውስጥ ያለው ዋነኛው ድክመት የግሉ ሚዲያ (በተለይም የሕትመት ሚዲያው) አሰራር በዝቅተኛ የጋዜጠኝነት ክህሎት ላይ ተመስርቶ የሚንቀሳቀስ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ይሔው ሚዲያ ከእጅ ወደ አፍ ባለፈ መልኩ የረጅም ጊዜ ሙያዊም ሆነ የንግድ ራዕይ በሌላቸው ሰዎች ታጭቋል፡፡ በዚህም ምክንያት አንደ ንግድ ሚዲያ አትራፊ ሆኖ ለመገኘት የሚያስችለውን ሁሉን አቀፍ ዝርዝር የዜና ዘገባ በማቅረብ የስርጭት አድማሱን ለማስፋትና አስተዋዋቂዎችን ለመሳብ የሚጥር አለመሆኑ ዋነኛ መለያ ባህሪው ሆኖ ይታያል፡፡ በንግዱ ህብረተሰብ ውስጥ በሚታየውና ነፃ የንግድ ውድድር ህግጋትን በመጣስ በአቋራጭ ለማደግ ያለው ስስትም

ምንም ጥረት በማያስፈልጋቸው ሃሚታዎች እና አሉባልታዎች ላይ እንዲረባረብ ይገፋፋዋል፡፡ በማስታወቂያ ላይ ከተመሰረተ ገቢ ይልቅም የገንዘብ ደጓሚዎች እንዳሻቸው የሚጋልቡት ልጓም አልባ የዱር ፈረስ መሆኑን ይመርጣል፡፡ ይህም በሚዲያ ጠበብት ዘንድ የጥገኝነት አባዜ (Resource dependence) የሚባለው ልክፍት የተጠናወተው፣ የፍርፋሪ ሰጪዎችን ፍላጐትና እምነት የሚያንፀባርቅ፣ ነፃነቱን አሳልፎ የሰጠ ኢንዱስትሪ እንዲሆን አድርጐታል፡፡ ይህ በግሉ የሚዲያ ዘርፍ ላይ የተንፀባረቀው ድክመት ሚዛናዊነትን በሚድያ ኢንደስትሪው ውስጥ እጅግ እንዲዳከም አድርጐታል፡፡

በሶስተኛነት የሚነሳውና በጋዜጣው ውስጥ የሚሳተፈው ጋዜጠኛ በአንዳንድ ጉዳዬች ላይ ያለው አረዳድ በሚዛናዊነት ላይ እንዴት የራሱን ተፅእኖዎች እንዴት እንደሚፈጥር አንድ ባንድ ለማየት እንሞክራለን ፡፡

ሀ) ጋዜጠኛው አንባቢውንና የዜና ምንጩን የሚያይበት መንገድ

ለ) ጋዜጠኛው በጋዜጣው ከሚቀርቡ መረጃዎች ጋር ያለው ግንኙነት

ሐ) የጋዜጠኞቹ ግላዊ ባህሪ እና የርዕዮተ አለም ዝንባሌ

ናቸው፡፡

ጋዜጠኛ አድማጩ ሚዛናዊ ነገር ይፈልጋል የሚል ሙያዊና ስነ-ምግባራዊ እምነት ካለው ሚዛናዊ ያለመሆን የራሱ ጣጣ ስለሚኖረው የግድ ሚዛናዊ ለመሆን ይሞክራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጋዜጠኛው ከሚያቀርበው መረጃ ጋር ያለው ግላዊ ቁርኝት ሚዛናዊ ከመሆን ሊያግደው ይችላል፡፡ እንደዚሁም ጋዜጠኛው በግል ባህሪው ጽንፈኛና ሁሉን ነገር ካልቀየርኩ የሚል ስርነቀል አቋም ያለው ከሆነ ይህ ርእዮተአለማዊ አመለካከቱ ከጋዜጠኝነቱ ጋር ያጋጩዋል፡፡ እንዲህ አይነቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የሰረፁ የተለመዱ ተግባራዊ መለኪያዎችን በሙሉ የሚያዋድቅ ሞገደኛና ፀለምተኛ አቋሙ በሙያ ክንዋኔው ሚዛናዊ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡ በመጨረሻም ጋዜጠኛው የራሱን ግላዊ

፣ ፖለቲካዊ ወይም ርዕዮተ አለማዊ ግብ ለማሟላት ሲል ሙያውን መጠቀሚያ መሳሪያ አድርጎ ለመንቀሳቀስ ከወሰነ ተቃራኒ እይታዎችና እውነታዎችን ነቅሶ ለሚያስቀረው የፕሮፖጋንዳ ስራው እንቅፋት እየሆኑበት ከፉኛ ከሚጠላቸውና ከሚጠየፋቸው እሴቶች ሚዛናዊነት ቀዳሚው ስለሚሆን ከቶም ቢሆን በጋዜጣውም ላይ ቦታ የማይሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

‹‹አዲስ ነገር›› ከዚህ ሁሉ አንፃር ስትገመገም እንዴት ትታያለች?

ሀ) ተቋማዊ ሁኔታ

አዲስ ነገር የተመሰረተችው ከተመሳሳይ ሙያ የፈለሱ ተመሳሳይ እድሜ ባላቸው፣ የተቀራረቡ የትምህርት ደረጃና ተመሳሳይ የፖለቲካ አቋም ባላቸው ሰዎች ነው፡፡ በርካታዎቹ አምደኞችና አዘጋጆች ቀደም ሲል የቤተ ክህነት ዲያቆናት የነበሩ፣ የማህበረቅዱሳን አባላትና በቅንጅት ዙሪያ የተሰባሰቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላትና ጠንካራ ደጋፊዎች የነበሩ ሰዎች ናቸው ፡፡ (በነገራችን ላይ ይህ የጋዜጠኞቹና የአምደኞቹ የወል ዲያቆናዊ ተሞክሮ እና ከማህበረ ቅዱደሳን ጋር ያላቸው ትስስር በጠቅላላ አለማዊ አመለካከታቸውና ፖለቲካዊ አበቃቀላቸው ላይ ካሳደረው ከባድ ተፅእኖ ባሻገር የጋዜጣዋ አንድ በጎ ገፅታ ለሆነው የቋንቋ ጥራትም ያበረከተው የጎላ ድርሻ ከፍተኛ ነው ፡፡ በአንዳንድ የጋዜጣዋ ሃያስያን እይታ በጋዜጣዋ ላይ ከመጠን አልፎ የሚታየውና የንግድ ምልክቷ እስከ መሆን የደረሰው 'እንቶኔ' እንዳለው ዘዬም ቢሆን ፋካውን ተከትለው ከተጓዙ መዳረሻው እዚያው ደጀ ሰላም ነው የሚሆነው ፡፡ 'ብነእ ወንሰተይ ወጌለመ ንመውት... እንዲል መፅሃፍ' ን የመሰሉ አንዳችም ስነ መለኮታዊ እውቀትንእና ጥበብን የማይጠይቁ መናኛና አልባሌ ጉዳዮችን ለበርካታ ታዳሚዎች ተደራሽ ባልሆነው የግእዝ ቋንቋ እየጠቀሱ ለመመሰጥ በሚሞክሩ አንዳንድ ግብዞች ዘንድ ተወዳጅና ተመራጭ ከሆነው የማጭበርበሪያ ዘዴ የተወሰደ ስምንተኛው የካርቦን ቅጂ አድርገው ነው የሚያዩት ፡፡ )

የአዲስ ነገርን ተቋማዊ ባህል ለመረዳት ጋዜጠኞቹ ማህበራዊ እውነታን እንዴት እንደሚያዩና እንደሚተነትኑ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ አይነቱ ግምገማ የተቋሙ አባላት የጀርባ ማንነት ቀጥተኛ አግባብነት ይኖረዋል ፡፡የአንድ የሚዲያ ተቋም ድርጅታዊ ባህል የሚፈጠረው አባል በሆኑት ጋዜጠኞች ተሳትፎም ጭምር ነውና፡፡ ድርጅታዊ ባህሎች ዴሞክራሲያዊ፣ ዘመናዊና ተራማጅ ከሆኑ የአባላቱን የሙያ ነፃነት የማጠናከር፣ ኋላቀር ፀለምተኛ ወይም አድሃሪ ከሆኑ ደግሞ በተቃራኒው አፍራሽ የሆነ ተፅእኖ የማሳደር ጉልበት አላቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በሕትመቶቹ ይዘት ላይ በጉልህ ተፅፎ የሚታየው የአዲስ ነገር ድርጅታዊ ባህል ፀረ ዴሞክራሲያዊ ፣ ሁሉን ኮናኝ (Nihilist) ፀረ-ስርአተኛ (anti establishment ) እና ጽልመተኛዊ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ የሚንቀሳቀሱበት ድርጅታዊ ባህልም ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን የማፍረስ ተልእኮና ግቦች ያሉት ጥርሱ ተበልቶ ያለቀ የአሮጌ ባህል መዘውር ተደርጎ ለወሰድ ይችላል ፡፡ ይህ የአዲስ ነገር ፀለምተኛና፣ ፀረ ሥርአት ዝንባሌ በዴሞክራሲያዊ አገሮች ፕሬሶች የመንግስትን ክንዋኔዎች በመተቸት ከሚያቀርቧቸው መጣጥፎች ጋር አንዳችም ተመሳሳይነት እንደሌለው መጤን ይኖርበታል፡፡ በነዚህ አገሮች ውስጥ ፕሬሶቹ የሚያቀርቧቸው ዘገባዎችና መጣጥፎች ከመንግስታዊ አካላት ፍላጎቶች ጋር የሚጋጩባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት እንዳልሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ግጭት ዴሞክራሲያዊ ተቋማትንና አሰራሮችን ለማረምና ለማሻሻል ባለመ ሂስ ላይ የተገነባ (Reformist antagonism) ገንቢና ተፈላጊ የሚዲያ ክንዋኔ እንጂ፣ እንደ አዲስ ነገር መጣጥፎች የራሱን የዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን ቁልፍ እሴቶችና ተቋሞች ለማጥፋትና ለመናድ ባነጣጠረ፣ አፍራሽ ተልእኮ የሚመራ አለመሆኑ ይታወቃል፡፡

አዲስ ነገር ግን ተጀምሮ እስከሚጨረስ (anti establishment) በሆኑ ሃሳቦችና ትንታኔዎች የታጨቀች ጋዜጣ ነች፡፡ ከዚያም በላይ በአዲስ ነገር ጋዜጣ በፀሃፊነት የሚሳተፉ ሰዎች ተመሳሳይ አቋምና አጀንዳ ያላቸው በመሆናቸው ከአንድ ጋዜጣ በሚጠበቀው የአመለካከት፣ የእይታ አብዛሃነትና ሚዛናዊነት በጋዜጣው ላይ ከቶም የማይታሰቡ ነገሮች ሆነዋል፡፡ ወጣም ወረደ ይህን

መሰሉ ተቋማዊ ባህል ባየለበት ሁኔታ ሚዛናዊ መሆን እንደማይቻል ይገባናል ፡፡ ከአዲስ ነገሮች የሚጠበቀው ጥንጥዬ እርምጃ ብትኖር ሁኔታውን በግልፅ አምኖና ተቀብሎ ንሰሃ መግባትና ሁኔታውን ለመለወጥ መጣር ነበር ፡፡ ይሁን እንጂ ይህን መሰሉን ተቋማዊ ግድፈት ተገቢ ለማድረግ የሚዛናዊነትን እሴት ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር ለማጋጨትና ተፃራሪ አድርጎ ለማቅረብ መሞከሩ ግን ገሃነም የሚያወርድ ድርብ ሃጥያት ነው የሚሆነው ፡፡ ይህን መሰሉ ከንቱ ጥረት ስርአቱን ለመናድ ካላቸው መርዘኛ ፍላጐት የሚመነጨው እና ከሁሉም ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ጋር የሚያላትማቸው የተጠናወታቸው ልክፍት ለፕሮፖጋንዳ ስራቸው መሰናክል ከሆነው ከዚህ ክቡር የሙያ እሴትም ጋር እንዳላተማቸው ከማሳየት ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም፡፡

## ለ) ኢንዱስትሪያዊ ሁኔታ

ከፍ ሲል ለማሳየት እንደሞከርኩት ገና ታዳጊ በሆነው የግል ሚዲያ ኢንዱስትሪ ውስጥ ተንሰራፍቶ ለሚታየው አጠቃላይ ችግር በስተቀር ( Exception ) ናቸው ከሚባሉ ጥቂት ጋዜጦች ውስጥ አዲስ ነገር የመካተት እድል አላገኘችም፡፡ ለታማኝ አንባቢያን ሽመታ ብቻ ታስበው በሚወጡ እና በሚዛናዊነት እጦት በሚሰቃዩት ሕትመቶቿ ከርዕየተ አለማዊ አጥሮች ባሻገር በሌሎች የአመለካከት ክፍሎች አባላትም ተነባቢ ለመሆን የሚያስችላትን ሙያዊ አሰራር አሻፈረኝ ማለቷ ሌላም የሚያሳየን ነገር አለ፡፡ የስርጭት መጠኗን (circulation) በማስፋት አስተዋዋቂዎችን ስባ ከማስታወቂያ በሚገኝ ገቢ ለመንቀሳቀስ የምትሻ ጋዜጣ አለመሆኗን ፡፡ ቀደም ሲል ግንቦት 7ን፣ የአንድነት ፓርቲን ፣ አሁን ደግሞ የመድረክን አላማና ግቦች በተለያዩ አቀራረቦች በግልፅ ማራመድ የተያያዘችው አዲስ ነገር የእነ ብርሃኑ ነጋን ፖለቲካዊ አላማ ለማስፋፋትና የፕሮፖጋንዳ ሥራ ለማከናወን በ97 ዓመተ ምህረቱ ምርጫ ዋዜማ ላይ ተፈጥራ ካነሳሳቸው አመፅ ጋር አብራ መቃብር እንደገባችው **አዲስ ዜና** ጋዜጣ ዘላቂና ቀጣይ የንግድ አላማ የሌላት መሆኑን ርዕዮተ አለማዊ ቃናዋና አፍራሽ ዝንባሌዋ በግልፅ ያመላክታል፡፡

### ሐ) የግለሰብ ጋዜጠኞቹ እይታ

ከስካሁኑ የጋዜጣዋ ክትትሌ እንደተረዳሁት አዲስ ነገር ላይ የሚጽፉት በርካታዎቹ ጋዜጠኞችና አምደኞች የዴሞክራሲያዊውን ስርአት ‹ተስፋ ቢስነት› ለማሳየት የሰበካ (advocacy) ስራ የተጠመዱ መሆናቸውን ነው፡፡ ከሚያቀርቧቸው ዜናዎችና ሃተታዎች እራሳቸውን ለይተው የማያዩ፣ ይልቁንም የክንዋኔዎች ዋነኛ ተዋናዮች በመሆን አጀንዳ በማቀበል ተቃዋሚዎችን ለመምራት የሚጥሩ ፤ ተሳዳቢና ተናዳፊ፣ ሚዛናዊነትን እንደ አንድ የሙያ እሴት የማይቀበሉ ናቸው፡፡ ለአብነት ያህልም አሰልቺ ፣መናኛና ገለባ ሀሳቦቹን የለአንዳች ሃፍረት ከፎተግራፉ ስር የሚያስነብበን (አሁን አሁንስ ማፈር ጀምሯል መሰል የፎቶውን ደብዛዛ አኬራ (ghost)ነው የሚያሳየን ) ታምራት ነገራ የተባለው የጋዜጣዋ ዋና አዘጋጅና አምደኛ በ97 ምርጫ ቅንጅትን ወክሎ በአዲስ አበባ ከተማ ለምርጫ የተወዳደረ ግለሰብ መጥቀስ ይቻላል ፡፡

እንግዲህ ጋዜጣዋ በዚህ ሁሉ ግድፈት በተጀቦደችበት ሁኔታ ሚዛናዊነት በህትመቷ ይዘቶች ውስጥ እንዴት ሊንፀባረቅ ይችላል? የሚለውን አስቺጋሪ ጥያቄ እና ብይኑን ለአንባብያን መተዉን እመርጣለሁ፡፡

በበኩሌ ግን አዲስ ነገሮች ከሚዛናዊነት ጋር የሚያላትሟችሁን ውስጣዊ ችግሮች ለማየት ድፍረቱ ኖሯችሁ የእነ እስክንድር ነጋንና ሲሳይ አጌናን ሙያ አሰዳቢ ና ብልሹ አሰራር ማወደስና የሚኒሊክና የኢቶድ ጋዜጦችን አርማ ማንገቡን ለማቆም ጥረት ብታደርጉ ከሙያውም ከራሳችሁም ጋር ለመታረቅ እድል ይኖራችኋል የሚል ትሁት ምክሬን በመለገስ ፅሁፌን እደመድማለሁ ፡፡

*በነገራችን ላይ፣ ይህ የጋዜጠኞቹና የአምደኞቹ የወል ዲያቆናዊ ተሞክሮ እና ከማህበረ ቅዱሳን ጋር ያላቸው ትስስር በጠቅላላ በአለማዊ አመለካከታቸው እና ፖለቲካዊ አበቃቀላቸው ላይ ካሳደረው ከባድ ተጽእኖ ባሻገር የጋዜጣዋ አንድ በጎ ገጽታ ለሆነው የቋንቋ ጥራትም ያበረከተው የጎላ ድርሻ አለው፡፡ በአንዳንድ የጋዜጣዋ ሃያሲያን እይታ በጋዜጣዋ ላይ ከመጠን አልፎ የሚታየውና የንግድ ምልክቱ እስከመሆን የደረሰው ‹‹እንቶኔ እንዳለው›› ዘዬም ቢሆን ፋካውን ተከትሎ ለተጓዘ ወደ ደጀ ሰላም ነው የሚያደርሰው፡፡ ‹‹ ንብነዕ ወንሰተይ ወኄለመ ንመውት....›› እንዲል መፅሃፉ አይነት ጥቅሶችን በግዕዝ እያንበለበሉ ምንም አይነት ስነ - መለከታዊ እውቀትና ጥበብን የማይጠይቁ መናኛና አልባሌ ነገሮችን ለበርካታ ታዲሚዎች ተደራሽ ባልሆነው የግዕዝ ቋንቋ እያጠቀሱ ለመመሰጥ የሚሞክሩ አንዳንድ ግብዝ ደብተራዎች ዘንድ ተወዳጅና ተመራጭ ከሆነው የማጭበርበሪያ ዘዴ የተወረሰ ወይም የተቀዳ አድርገው ነው የሚያዩት፡፡*